# 1 \section{ይህ አርእስት ነው}

የሆሄያት ግጥጥሞሽ ቃል ያበጃል ፤ የቃላት ስኬት ዐረፍተ ነገር ይመሠርታል ፤ የዐረፈተ ነገራት ስብስብ አንቀጽ ይገነባል። አንድ አንቀጽ ከሌላው በነፃ ቦታ ይለያል።

በአቀማመጥ ረገድ ፥ ማንኛውም አንቀጽ የሚከተሉት የጋራ ጠባዮች አሉት። ጹሑፉ በጋራና በቀኝ የሚነሳበትና የሚያርፍበት ዳር አለው ፤ የመጀመሪያው መስመር የሚነሳበት ነፃ ክፍት ቦታ ይኖረው ይሆናል ፤ በያንዳንዱ መስመር መካከል የተመጠነ ክፍት የነፃ ቦታ አለ ፤ እናም ሌሎችም ይገኙበታል። የጠርዝ ማስታወሻና አቀማመጡ።

1. የመጀመሪያው ዝርዝር ይኸን ይመስላል ፤
2. የሚቀጥለው መስመር እንደሚታየው ፤
3. እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

የዝርዝር ዓይነት በደፈናው በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው በተራ ቊጥር ወይም በሆሄ ሲዘረዝር ፥ ሁለተኛው ግን በክብ ምልክት ወይም በመሳሰለው ይዘረዘራል። ዝርዘራ ደራጃ አለው። አንድ ዝርዝር በውስጡ ሌላ ዝርዝር ከሌለው ደረጃው ፩ኛ ይሆናል ፤ ነገር ግን በውስጡ ሌሎች ዝርዝሮች ካሉት እንደጥልቀታቸው ይሰየማሉ፦ ፩ኛ ፥ ፪ኛ ፥ ፫ኛ ፥ እያለ ይቀጥላል። የሚቀጥለው ምሳሌ ሁለት ደረጃ አለው።

1. ይህ በ፩ኛ ደረጃ የሚገኘው ዝርዝር ነው። ውጫዊ ዝርዝር ብለን ልንጠራው እንችላለን።
   (a) ይህ በ፪ኛ ደረጃ ያለ ዝርዝር ነው። ውስጣዊ ዝርዝር ብለን ልንጠራው እንችላለን።
   (b) የተራ ቊጥር የመስጠቱ ኃላፊነት የላተክ ነው።
2. በአጠቃላይ ደረጃ የዝርዝር አጻጻፍ ይኸን ይመስላል።

በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ሌሎች ጽሑፎችን መጥቀስ የተለመደ ነው። ከዋናው ጽሑፍ ለይቶ ማሳየት ተነባቢነቱን ይጨምራል ፤ እንዲሁም መልኩን ያሳምራል። የጥቅስ አቀማመጥና መልኩ፦

> “. . . መምህርና መጽሐፍ የተማሪ በት ፥ እንዚህ በ፫ቱ በጥሩ ምንጭና በፈሳሽ በወራጅ ፥ ተማሪና ጣፊም በውሃ ቀጅ ይመሰላሉ ፤ በጥፈትና ባነጋገር የፊደል ጥንቃቄ ከሌለ ግን ምንጩ ደፈረሰ ማለት ነው።. . .”
>
> –አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ሌሎች ጽሑፎችን መጥቀስ አንዱ መንገድ ሲሆን ሌላኛው ግን ለአንድ አባባል ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት ከተፈለገ ፤ ወይም ምንጩን ማመልከት አሥፈላጊ ከሆነ ፤ ወይም የአንድን ነገር ምንጭ ከጽሑፍ ጋር አስተሳስሮ መጻፉ ተነባቢነቱን ይቀንሳል ተብሎ ከታሰበ ፤ የግርጌ ማስታወሻ አብይ አማራጭ ነው። ለምሳሌ ከላይ የተሰጠው ጥቅስ ከአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መሆኑ ይታያል ፤ ነገር ግን የመጽሐፉ አርእስት አልተሰጠም። የግርጌ ማስታወሻ በመጠቀም ያንን ማድረግ ይቻላል። በመሆኑም [1] ። ግጥም ለሒሊና።

ባለፍኩበት ጐዳና እነሱ ተነሱ ፤
እኔስ ሰግቻለሁ አፈር እንዳይለብሱ።
ግን ይሉኛል እነሱ ከለበስን ቆየ ፤
የሁለቱ ትርጒም እንደገና ካልተለየ።

[1] መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ፤ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፤ ታተመ በአለቃ ደስታ ተክለ ወልድ ፤ ፲፱፻፵፰ ዓምተ ምሕረት።